# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 07-12- 2011 تاريخ
Date:

Lakk.: 009/stm-abo/ 2011 رقم
No.:

## *የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የሁሉንም ሃይማኖቶች እኩልነትና ክብር ይንከባከባል*
*(የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫ)*

የወያኔ መንግስት ከኦሮሞ ህዝብ ኣንድነት ከፍተኛ ስጋት ኣለው። ይህን ያህል ሰፊ የሆነ ኣንድ ህዝብ ኣንዲት የጋራ ሃገርና ኣንድ የጋራ እድል ያለው ከመሆኑ የበለጠ ወያኔን የሚያሳስበው ያለም ኣይመስልም። ከዚህም በመነሳት የዚህን ህዝብ ኣንድነት ለመሸርሸር ያላደረገው ጥረት የ ለም። ዋናው የኦሮሞ ህዝብ ኣቅም ጥንካሬ ኣንድነቱ ስለሆነ ይህን ኣንድነት ኣላልቶ ህዝቡ ለዘላለም ከጭቆና ቀንበር እንዳይላቀቅ ማድረግ ምንጊዜም ቢሆን የኦሮሞ ጠላቶች ህልም ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ጠላቶች፣ በተለይም ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወያኔ፣ ይህን ሰፊ ህዝብ በኣ ካባቢ ወይም በጎሳ ለመከፋፈል ለረጂም ዘመናት ያደረጉት ጥረት ቢከሽፍባቸውም ዛሬም ተስፋ ቆርጠው ኣደብ ገዝተው መቀመጥ ኣልተቻለላቸውም። የወያኔ መንግስት በሃይማኖት ኣማካኝ ነትም የተቻለለትን የትንኮሳ ኣይነት ሁሉ ተጠቅሞ የኦሮሞን ህዝብ ኣንድነት ለማላላት ከመድከ ም ተቆጥቦ ኣያውቅም። የኦሮሞ ህዝብ የተለያዩ እምነቶች ተከታይ በመሆኑ ምናልባት በዚህ መንገድ የሚሳካለት መስሎት ስውር ጠላታዊ ዘመቻውን ተያይዞታል።

ወያኔ የክርስትና ወይም የእስልምና እምነት ተከታይ ወገን በሚበዛባቸው የኦሮሚያ ኣካባቢዎች ኦነግ የዋቀፋና ሃይማኖት ለማስፋፋት የቆመ በማስመሰል ይሰብካል። ይህም የክርስትና ወይም የ እስልምና ሃይማኖት ተከታይ በሆነው የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ኦነግ እንዲጠላ ለማድረግ ታስቦ መሆኑ ነው። የእስልምና ወይም የዋቀፋና እምነት ተከታዮች በሚበረክቱባቸው ኣካባቢዎች ደግሞ ኦነግን የክርስትና ሃይማኖት ድርጅት በማስመሰል ጠላታዊ የፍብረካ ወሬውን ይነዛል። ይህም የ እስልምናና የዋቀፋና እምነት ተከታዮች ኦነግን በጥርጣሬ እንዲመለከቱትና ድጋፋቸውን እንዲ ነፍጉት ለማድረግ የታለመ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የክርስትና ወይም የዋቀፋና ሃይማኖት ተከ ታዮች የጎላ ቁጥር ባላቸው ኣካባቢዎች ኦነግ ለእስልምና ሃይማኖት የቆመ ድርጅት ኣስመስሎ ያስወራል። በዚህ ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ የኦሮሞ ህዝብን ኣንድነት ከተቻለ የመናድ ካልተቻለም የ ማላላት ተልእኮ ኣንግበው የተሰማሩ የወያኔ ተላላኪዎች ቁጥር የዋዛ ኣይደለም።

በግልፅ ሊታወቅ የሚገባው ሃቅ ግን፣ ኦነግ ማለት ወያኔ በዚህ መልኩ ሊያቀርብ የሚሞክረው ኣ ይነት ድርጅት ኣይደለም። ኦነግ ማለት ለኣንዱ ሃይማኖት ወግኖ የተቀሩትን ወደ ዳር የሚገፋ ድርጅት ኣይደለም። ኦነግ በሁሉም ሃይማኖቶች እኩልነት ያምናል። በድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ገፅ 10 ኣንቀፅ 5.8 ስር በግልፅ እንደተቀመጠው "*መንግስት ሃይማኖትን ወደ ዳር ኣ ይገፋም፣ ለማንኛውም ሃይማኖት ኣያዳላም። የሁሉም ሃይማኖቶች እኩልነትና ክብር ይጠበቃል*" ይላል። በዚህ ኣንቀፅ ስር "*መንግስት*" ተብሎ የተቀመጠው በኦነግ የፖለቲካ ፕሮግራም መሰረት ወደፊት የሚመሰረተውን የኦሮሚያ መንግስት ለማመልከት ነው።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የሚታገልለትን ህዝብ ማንነት ጠንቅቆ ይረዳል። የኦሮሞ ህዝብ ኣንድ ህዝ ብ ሆኖ የተለያዩ እምነቶች የሚከተል መሆኑ ከኦነግ የተሰወረ ኣይደለም። የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ ለሆነው ለዚህ ህዝብ ከሃይማኖት ገለልተኛ የሆነ ፖሊሲ የመከተል ኣስፈላጊነትም ኣያጠ ያይቅም። የኦሮሞ ህዝብ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ መሆኑ ደግሞ በይበልጥ የህብረተሰቡን ውበትና ኣለማቀፋዊ ኣመለካከት ያሳያል እንጂ የሚያሳስብ ነገር ኣይደለም። ኣንድ ህዝብ ኣንድ

P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea | Telefax 291 1 153886 | E-mail abamilki@gemel.com.er

የጋራ ሃይማኖት ተከታይ ስለሆነ ብቻ ኣንድነቱ ኣስተማማኝ መሰረት ኣለው ሊባል ኣ ይችልም። ወይም የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ በመሆኑ የኣንድነቱ መሰረት ለስጋት የ ተጋለጠ ሊባል ኣይችልም። ኣንድ የጋራ ሃይማኖት ተከታይ መሆን ብቻውን የሰላምና የኣንድነት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ሩቅ ሳንሄድ እዚሁ ጎሮቤታችን ሶማሊያ ውስጥ ከሚታየው እውነታ በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል። ወሳኙ ነገር የኣንድን ሃገር ፖለቲካ የ ሚመሩ ወገኖች የሚከተሉት ፖሊሲ ኣይነት እንጂ የህዝቡ የሃይማኖት ኣንድነት ወይም ልዩነት ጉዳይ ኣይደለም።

ይህን ሃቅ ይበልጥ ለማረጋገጥ ህንድና ፓኪስታንን እንደ ምሳሌ ወስደን ማየት እን ችላለን። ዛሬ ኣስተማማኝ ሰላምና ፈጣን ልማት የሚታየው ከፓኪስታን ይልቅ በህንድ ነው። እንደ ሃይማኖት ስብጥር ካየን የፓኪስታን ህዝብ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻልበት መልኩ ኣንድ የጋራ ሃይማኖት ተከታይ ነው። የህንድ ህዝብ ደግሞ የተለ ያዩ እምነቶች ተከታይ ነው። የሃይማኖት ኣንድነት የሰላምና የልማት ዋስትና ቢሆን ኖሮ ከህንድ በላቀ መልኩ ፓኪስታን ሰላማዊና ልማታዊ ሃገር በሆነች ነበር። ነገር ግን ዛሬ በነዚህ ሃገራት የምናየው እውነታ የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀ ሰው ወሳኙ ነገር የሃይማኖት ኣንድነት ወይም ልዩነት ላይ ሳይሆን ለየትኛውም ወገን የማያዳላና የሁሉንም ሃይማኖቶች ተከታይ ህዝብን በኣንድ ኣይን የሚመለከት የፖለቲካ ፖሊሲ መከተሉ ላይ ነው። የኦሮሞ ነፃነት ግንባርም እንደ ታጋይ ድርጅት በዚህ ያምናል። ነገም እንደ መንግስት ከዚህ የተለየ ፖሊሲ ሊከተል ኣይችልም።

የኦሮሞ ህዝብ የኣንድነቱ ዋልታና ማገር የሆኑ የጋራ እሴቶች ኣሉት። ከጋራ እሴቶቹ በተጨማሪ ደግሞ ተመሳሳይ የጭቆና ታሪክ ያለው ህዝብ ነው። በኦሮሞ ህብረተሰብ ውስጥ ኣንገብጋቢው ርእሰ-ጉዳይ እንዴት እንደ ህዝብ ከተጫነብን የጭቆና ኣገዛዝ እን ላቀቅ የሚል እንጂ በሃይማኖት ኣይነት ሳቢያ መቀራረብ ወይም መናቆር ኣይደለም። ጠላት ይህንን ሃቅ ባለመገንዘቡ የሃይማኖት ልዩነቶችን ኣራግቦ በቀላሉ የኦሮሞን ኣንድ ነት መናድ የሚሳካለት ይመስለዋል። ይህን ስንል ግን ወያኔ በሚፈልገው መልኩ በኦሮሞ ህብረተሰብ መካከል የሃይማኖት ልዩነቶችን ማራገብ ስራቸው ያደረጉ ኣንዳንድ ወገኖች የሉም ማለት ኣይደለም። እነዚህ ወገኖች በሃይማኖታዊ መርሆዎች ብቻ ተማር ከው ስለ ብሄራዊ ኣንድነት ለማሰብ ጊዜ ኣጥተው ሊሆን ይችላል። ወያኔ የነዚህን ወገኖች ድክመትና የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ኣናሳነት እንደ መሳሪያ በመጠቀም ኦሮሞን በሃይማኖት ለመከፋፈል ደፋ ቀና ሲል ማየት የሚያስገርም ኣይሆንም። ይሁን እንጂ ከህዝቡ መሃል እጅግ ብዙሃኑ የየራሱን እምነት ኣጥብቆ እንደሚከተል ሁሉ በኦሮሞነቱ ሲመጡበትም ለማንኛውም የጠላት ከፋፋይ ሴራ ከቶ የማይበገር የና ኣቋዋም እንዳለው መታወቅ ኣለበት። በስልጣን ላይ ያለው ስርኣት ራሱን የሃይማኖት መብቶች ኣክባሪ እ ያስመሰለ በኣንድ ሃይማኖት ተከታዮች መካከልም ሳይቀር ልዩነቶችን ለማራገብ እንደሚ ሰራ እየተጋለጠ በመሄድ ላይ ነው።

ኦነግ በድርጅታዊ ታሪኩ ያጋጠሙትን ኣንዳንድ ሃይማኖት-ነክ ተግዳሮቶችን በድል ተወጥቶኣል። ኣንጋፋ የድርጅቱ ታጋዮች በ1978 በምስራቁ የትግል ሜዳ ትከስቶ የ ነበረውን መሰል ችግር ሊቀለብሱ የቻሉት ድርጅታቸው ኦነግ በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ ባለው የገለልተኛነት (secularity) ኣቋዋም ላይ በመፅናታቸው ነው። እንዲሁም በ1980 የኦነግ ከፍተኛ ኣመራር ለስራ ጉዳይ ወደ ጎሮቤት ሶማሊያ በመንቀሳቀስ ላይ ሳለ ሽ ኒጋ በተባለች በረሃማ ስፍራ ባጋጠሙት የሶማሊ ሽፍቶች የህይወት ፈተና ቀርቦለት

ነበር። እነዚያ ሽፍቶች የኣንድ ኦሮሞ ልጆችን በሃይማኖት ልዩነት ለሁለት ከፍለው ኣንዱን ወገን ለመግደል በዛቱበት በዚያች ወቅት ታጋዮቹ ለዘላለም በምሳሌነቱ ሲወሳ የ ሚኖር ታሪክ በጋራ በማስመዝገብ ኣንድ ላይ ተሰዉ። *“እኛ ሙስሊምና ክርስቲያን ተብለን ኣንከፋፈልም! እኛ ኦሮሞ ነን! ኣንድ የጋራ እድል ኣለን! ለኣንድ የጋራ ኣ ላማ ስንል ከቤታችን ወጣን፥ ለኣንድ የጋራ ኣላማም እንሰዋለን!!’* በማለት ነበር የ ኦሮሞን ኣንድነታዊ ጥንካሬ ለማረጋገጥ ሲሉ መተኪያ የሌላት ህይወታቸውን መስዋእት ያደረጉት። የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ዛሬም ሆነ ነገ እንደዚህ ባሉት በኣላማቸው የኑ ታጋዮቹ ይገለፃል!!!

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

ታይሳስ 2011